
© IOM 2018

# VOLUNTARY RETURN HOME

ወደ አገርዎ ለመመለስ እያሰቡ ነው?
በፈቃደኝነት እንዲመለሱ ልንረዳዎ እንችላለን።
Fedasil የመልስ ጉዞዎን ያስተባብራል እና
የገንዘብ ወጪ ይሸፍናል። እንዲሁም አንድ
ላይ ሆነን በአገርዎ ውስጥ እንዴት ልንረዳዎ
እንደምንችል እንመረምራለን።

0800 32 745 (free number)
www.voluntaryreturn.be

fedasil
FEDERAL AGENCY FOR THE RECEPTION OF ASYLUM SEEKERS

Co-funded by the European Union

1

## በፈቃደኝነት መመለስ ምንድነው?

ወደ ትውልድ አገርዎ መመለስ ማለት ነው። እናም የመልቀቅ ውሳኔውን የሚወስኑት እርስዎ ነዎት። ጉዞው ከመደበኛ ተሳፋሪዎች ጋር ተመሳሳይ ነው። ባለስልጣናቶቹ ከመድረስዎ በፊት እንዲያውቁ አይደረግም። እርስዎ ላለመልቀቅ ለመወሰን ሁልጊዜም ነጻ ነዎት።

2

## በፈቃደኝነት ለመመለስ እንዴት ማመልከት እችላለሁ?

በቤልጂየም ውስጥ ከሚገኙ ብዙ የግንኙነት ጣቢያዎች ውስጥ አንዱን ማነጋገር፣ ስለ ጉዳዩ ማህበራዊ ሰራተኛዎን ማነጋገር ወይም ከክፍያ ነጻ በሆነው ቁጥር በ 0800 327 45 መደወል ይችላሉ።

3

## የእኔን መመለስ የሚያስተባብረው ማነው?

Fedasil በፈቃደኝነት የመመለስ ፕሮግራሙን የማስተባበር ኃላፊነት አለበት። አለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት (IOM) የመመለስ ፕሮግራሙን በአውሮፕላን - ወይም ለአንዳንድ አገሮች በአውቶቡስ ያደራጃል። አገር ከደረሱ በኋላ የሚደረግ እርዳታን የተመለከተ ኃላፊነት የ IOM እና Caritas International ነው።

4

## መክፈል ያስፈልገኛል?

አይ፣ መክፈል የለብዎትም። Fedasil ለአውሮፕላን ወይም ለአውቶቡስ ትኬት እንዲሁም ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ወይም ወደ ጣቢያው ለሚደረግ ጉዞ ይከፍላል። ከቆንስላ ቢሮዎች የራስዎን የጉዞ ሰነድ መውሰድ ያለብዎ ሲሆን ሊከቁ ሲሉ ለዚህ ያወጡት ገንዘብ ተመላሽ ይደረግልዎታል።

5

## ከእኔ ጋር ምን ያህል ሻንጣ መያዝ እችላለሁ?

የአየር መንገድን ወይም የአውቶቡስ ኩባንያዎችን የሻንጣ ገደብ ማክበር አለብዎት፤ ለአንድ ሰው የሚፈቀደውን የሻንጣዎች ብዛት ወይም ከፍተኛ ክብደት አይለፉ። ስለዚህ እራስዎን መገደብ አለብዎት !





6

## በጉዞው የሚሸኝ ወይም አብሮ የሚጓዝ ሰው አለ?

አዎ፣ ከቤልጂየም በሚነሱበት ጊዜ ከ IOM የመጣ ሰው ከእርስዎ ጋር ይገናኝ እና የአውሮፕላን ቲኬትና ማንኛውንም ተቆራጭ ይሰጥዎታል ከዛም ወደ ድንበር ቁጥጥር ጣቢያ ድረስ ይሸኝዎታል። ከፈለጉ፣ ሌላ ሰው ወደ ትውልድ አገርዎ ሲደርሱ እዛ ሊጠብቅዎት ይችላል። እንዲታወቁ የ IOM የፕላስቲክ ሻንጣ እንዲይዙ ይጠየቃሉ።

7

## በአገሬ ውስጥ ኑሮ ቀላል አይደለም እናም ምን አይነት ድጋፍ ልታቀርቡ ትችላላችሁ?

እርስዎን በመልሶ መቀላቀል ጉዞዎ ሊረዱ ከሚችሉ በትውልድ አገርዎ ውስጥ ከሚገኙ አጋር አካላት ጋር በትብብር እንሰራለን። ይህ ምናልባት የእርስዎን የጤና ወጪዎች መሸፈንን፣ ስራዎን መደገፍ፣ የራስዎን የንግድ ሥራ መጀመርን ሊያካትት ይችላል። ይህ እርዳታ ለሁሉም ሰው የሚሰጥ አይደለም፣ እያንዳንዱ ጉዳይ የተለየ ነው። የትኛው አይነት እርዳታ ማግኘት እንደሚችሉ ለማወቅ እባክዎን ተጠሪዎን ያነጋግሩ። እንዲሁም ከመልቀቅዎ በፊት የተመላሾች ተቆራጭ ይሰጣል።

*This brochure is intended for foreigners without a residence permit in Belgium. It is available in 19 languages: Albanian, Amharic, Arabic, Bulgarian, Chinese, Dutch, English, Farsi, French, Lingala, Mongolian, Pashto, Portuguese, Fula, Russian, Serbian, Slovak, Spanish and Tigrinya. You can download the different language versions on www.retourvolontaire.be/fr/partners.*

# CONTACT US.

www.voluntaryreturn.be/contact-us



fedasil

FEDERAL AGENCY FOR THE
RECEPTION OF ASYLUM SEEKERS